# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና

# ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 1-10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከጃንዋሪ 11-20 እና ከጃንዋሪ 21-31/ 2025

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 2025

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ


እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ....- 1 -

ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ....- 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት....- 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....- 3 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 4 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 5 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ....- 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20, 2025 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ....- 6 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....- 6 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ....- 7 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 7 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 8 -




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

በጃንዋሪ የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተጠናክሮ ተስተውሏል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በአንዳንድ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም በአዴት 3.2፤ በአዲግራት 3.5፣ 4.5፤ በሐሮማያ 3.8፣ 3.6፣ 2.2፣ 0.2፣ 4.0፤ በአለም ከተማ 3.8፣ 3.2፣ 3.0፣ 4.0፣ 4.0፣ 4.0፤ በአምባማሪያም 4.4፣ 4.6፣ 4.6፣ 4.5፣ 3.8፣ 4.4፣ 4.0፣ 4.6፤ በአርሲ ሮቤ 3.4፣ 3.0፣ 2.5፣ 3.0፣ 4.0፤ በባቲ 4.6፣ 3.6፣ 3.6፤ ቦሬ4.5፤ በቡኢ 3.0፣ 3.8፣ 3.4፣ 2.8፣ 3.0፣ 3.4፣ 4.0፣ 4.6፤ በደብረብርሀን -2.0፣ 1.4፣ 3.6፣ 3.0፣ 1.2፣ 2.0፣ 3.8፤ በዳንግላ 3.5፣ 4.8፣ 4.5፣ 4.7፣ 4.5፣ 4.5፣ 4.0፤ በደባርቅ 4.2፣ 4.0፣ 4.2፣ 4.8፤ ደብረ ወርቅ 4.4፤ በቢሾፍቱ 3.0፣ 2.0፣ 2.4፣ 4.0፣ 2.0፣ 3.2፤ በእነዋሪ 4.0፣ 4.0፣ 4.5፤ በፍቼ 4.5፤ በጉንዶ መስቀል 4.4፤ በእምድብር 3.4፤ በጃራ 4.0፣ በጅግጅጋ 1.0፣ 4.0፣ 4.2፤ በጅማ 2.4 ፤በማይጨዉ 4.0፤ በመሐል ሜዳ 1.5፣ 4.2፣ 2.2፣ 4.5፤ በሮቤ ፤ በሾላ ገቢያ 1.0፣ 2.1፣ 3.0፣ 2.0፣ 3.0፣ 2.1፣ 3.1፣2.1፣ 3.8፣ 4፤ በወገል ጤና -1.0፣ 2.0፣ 1.6፣ 2.0፣ 2.5፣ 4.0፤ በወረኢሉ 4.8፣ 3.6 እንዲሁም የትኖራ 4.1 በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1) ፡፡

በሌላ በኩል በጥቂት የደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጨረሻዎቹ አምስት ቀናት ከነበረዉ የደመና ሽፋን ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መከከለኛ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በስኮሩ 15.5፣ በማሻ 10፤ እንዲሁም በአማን 5.6 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በስኮሩ 15.5፣ በማሻ 10፤ እንዲሁም በአማን 5.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ እንዲሁም አብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍል በደረቃማው የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል፡፡ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከጥቂት የደቡብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ቦታዎች በስተቀር ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የጃንዋሪ የመጀመሪያዉ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በመኸር አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታ ነበረዉ። ከደረቃማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛው፣ የደቡብና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ መጠነኛ ቅዝቃዜ ተስተዉሏል፡፡ በሌላ በኩል በመጨረሻዎቹ ቀናት በጥቂት የደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ኪስ አካባቢዎች ላይ የነበረው መጠነኛ እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ  አስተዋጽኦ ነበረው (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች በደረቅ እና ከፊል ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር እንደነበሩ የተተነተኑ የውኃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ሆኖም በጥቂት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ማለትም በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ እና በመካከለኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ ለውሃ ሀብት መጠነኛ አስተዋፅዖ እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል የተቀሩት ተፋሰሶች በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ አይሻ፣ አፋር ደናክል፣ መረብ ጋሽ እና ኦጋዴን፣ የበጋው ደረቅ ሁኔታ ስር ቆይተው ነበር (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በጥቂት የመካለኛው፣ በምሥራቅ፣ በሰሜን ምሥራቅ፤ በሰሜን ምዕራብ እንዲሁም በደቡብ ኢትዮጵያ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አንጻራዊ የእርጥበት መጠንና የደመና ሽፋን መጨመር እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7) ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የደቡብ ኦሮሚያ፤ ሲዳማ፤ ደቡብ ምዕራብ እና የምዕራብ አከባዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለና መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7) ፡፡

በሌላ በኩል አሁን ላይ እየተስተዋለ ያለው የበጋው ደረቅ፤ ጸሀያማ እና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ በሚቀጥሉት ቀናትም ቀጣይነት እንደሚኖረው አህዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20, 2025 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመጪዎቹ የጃንዋሪ አስራ አንድ ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሀያማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ይስተዋላል፡፡ በሌላ በኩል በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚፈጠሩት  ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ላይ በመነሳት በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ ፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ለድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት የሚኖረውን ምቹ የአየር ሁኔታ በመረዳት የተሰበሰቡ ሰብሎችን አጠናቆ የመውቃትና የማጓጓዝ ስራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል። በተለይም የበልግ አብቃይ የሆኑ አካባቢዎች የሰብል ማሳዎችን ከማንኛወም ተረፈ ምርት ከአሁኑ ነጻ የማድረግ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል። በሌላ በኩል በሳምንቱ የመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ በጥቂት ኪስ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የምሥራቅ፣ የሰሜን ምስራቅና የመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት የሚጠበቅ ሲሆን ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች መጠነኛ የግጦሽ ሳር እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በማሻሻል አዎንታዊ ሚና የሚኖረዉ ሲሆን በሌላ በኩልም የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ከማዘጋጀት አንጻር ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ጃንዋሪ ሁለተኛ አሥር ቀናት አብዛኛው ተፋሰሶች ላይ በደረቅ የእረጥበት ሁኔታ ስር ሆነው ይቆያሉ፡፡ ይሁን እንጂ በጥቂት ላይኛው ተከዜ፣ አፋር ደናክል እንዲሁም በጥቂት ላይኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ያገኛሉ። ይህም ሁኔታ የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በጥቂቱም ቢሆን እንደሚያሻሻሽል ይጠበቃል። በአንጻሩ በአብዛኛዉ አዋሽ፣ አይሻ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ኦጋዴን እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን በእነዚህ አካባቢዎች ላይ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ያለውን የውኃ ሀብት ከብክነትና ከብክለት ጠብቆ በአግባቡ መጠቀም ይገባል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et